የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 27
ADDIS ABABA, 5th March, 2025

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፷፱/፪ሺ፲፯

የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……….........................................ገጽ ፲፯ሺ፯፻፳፱

## Content

Regulation No. 569/2025

Ethiopian Defense University Establishment Regulation ……………..………...Page 17729

### ደንብ ቁጥር ፭፻፷፱/፪ሺ፲፯

### <u>የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚኒስትሮች ምክር ቤት በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፮/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና አንቀጽ ፹፬፣ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፷፱/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

### REGULATION No. 569/2025

### <u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN DEFENSE UNIVERSITY</u>

The Council of Ministers of the Federal Democratic Republic of Ethiopia issued this Regulation in accordance with Sub-Article (8) of Articles 25 and 84 of the Defense Forces Proclamation No. 1286/2023; and Sub-Article (1) of Article 5 of the Higher Education Proclamation number 1152/2019.

### <u>PART ONE</u>

### <u>GENERAL</u>

1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as the “Ethiopian Defense University Establishment Regulation No. 569/2025”.

2. <u>Definition</u>

In this Regulation unless the context otherwise requires:-

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ **"መንግሥት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ነው፤

፪/ **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መከላከያ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፫/ **"አዋጅ"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ ነው፤

፬/ **"ዩኒቨርሲቲ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ መሰረት የተቋቋመ የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ነው፤

፭/ **"ቦርድ"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሰረት የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲ ቦርድ ነው፤

፮/ **"ሴኔት"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ መሰረት የተቋቋመው የዩኒቨርሲቲ ሴኔት ነው፤

፯/ **"ፕሬዝዳንት"** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሰረት የሚሾም የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊ ነው፤

፰/ **"ዋና ዳይሬክተር"** ማለት በምክትል ፕሬዝዳንት ማዕረግ በኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ስር ለሚደራጅ ኮሌጅ ወይም ኢንስቲትዩት የበላይ ኃላፊ ነው፤

፱/ **"ዲን"** ማለት በኮሌጁ ስር የሚደራጅ የአካዳሚክ ወይም የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን የሚመራ ኃላፊ ነዉ፤

፲/ **"ዳይሬክተር"** ማለት በዲን ደረጃ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተመድቦ የሚሰራ ኃላፊ ነው፡፡

፲፩/ **"የአካዳሚክ ሰራተኛ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ የያዘ ነው፤

1/ **"Government"** means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2/ **"Ministry" or "Minister"** means the Ministry or Minister of Defense of the Federal Democratic Republic of Ethiopia respectively;

3/ **"Proclamation"** means the Higher Education Proclamation No. 1152/2019;

4/ **"University"** means the Ethiopian Defense University established in accordance with Article 3 of this Regulation;

5/ **"Board"** means the University Board established in accordance with Article 6 of this Regulation;

6/ **"Senate"** means the University Senate established in accordance with Article 8 of this Regulation;

7/ **"President"** means the head of the University to be appointed in accordance with Article 12 of this Regulation;

8/ **"Executive Director"** means the head of, with the title of Vice President, the College or Institute to be organized under the University;

9/ **"Dean"** means the head of academic or research and community service activities of the Colleges organized under the University;

10/ **"Director"** means the head who is assigned to different departments of the university at the level of dean;

11/ **"Academic Staff"** means as defined in Sub-Article (3) of Article 2 of the Proclamation;

፲፪/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፫/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠው አገላለጽ የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፫. <u>መቋቋም</u>**

፩/ የኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ዋና አድራሻ ቢሾፍቱ ሆኖ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ወይም ከሀገር ውጪ የራሱን ማዕከላት ወይም ቅርንጫፎች ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፫/ ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**፬. <u>ዓላማ</u>**

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ዕውቀትን ማዳበር፣ ማስፋፋትና ማስተላለፍ፤

፪/ የሰራዊቱን የውጊያ አቅምና ዘመናዊነቱን በሚያጎለብቱ እና ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጭብጦች ላይ የምርምርና ልማት ሥራዎችን መስራት እና ማሸጋገር፤

፫/ በቴክኖሎጂ፣ በጤና፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በወታደራዊ ሳይንስ እና በሌሎች የሙያ መስኮች ትምህርት እና ስልጠና መስጠት፤

፬/ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት፣ የማማከር ሥራ መስራት እና ለመከላከያ ተቋማት ቀጥተኛ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፡፡

**፭. <u>የዩኒቨርሲቲው ሥልጣንና ተግባር</u>**

ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

12/ **"Person"** means a natural or juridical person;

13/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Establishment</u>**

1/ The Ethiopian Defense University (hereinafter referred to as the "University") is established by this Regulation as an autonomous higher education institution having its own legal personality.

2/ The university shall have a head office in Bishoftu and may have centers or branches elsewhere in the country or abroad.

3/ The University shall be accountable to the Ministry.

**4. <u>Objective</u>**

The University shall have the following objectives:-

1/ Develop, expand, and transfer knowledge;

2/ Conduct and transfer research and development activities that can develop the military defense capacity and issues that have national strategic importance;

3/ Provide education and training in Technology, Health, Social Science, Military Sciences, and other professional fields;

4/ Provide community service, consultancy, and direct professional support to Defense institutions.

**5. <u>Powers and Duties of the University</u>**

The University shall have the following powers and duties:

፩/ የመከላከያን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችሉ የቅድመ ምረቃ እና የድህረ-ምረቃ ትምህርት መርሐ-ግብሮችን ይቀርጻል ይሰጣል፤

፪/ የምርምር ጭብጦችን በመለየት የመከላከያን እና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ የምርምር ውጤቶችን ማሸጋገርና የማህበረሰብ አገልግሎት ይሰጣል፤

፫/ የመከላከያን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን ይቀርጻል ይሰጣል፤

፬/ በቅድመ-ምረቃ እና ድህረ-ምረቃ ትምህርት ለሚሰጡ የመከላከያ ኮሌጆች፣ ኢንስቲትዩቶች እና አካዳሚዎች የተማሪ ቅበላን፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ስርዓትን፣ የትምህርት ፕሮግራምና ቀረጻ ሥራዎችን፣ የተማሪ መረጃ አያያዝ ስርዓትን ይመረምራል፤ ያጸድቃል፣ እንዲሁም የትምህርት ማስረጃ ይሰጣል፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ የተደነገገውን ለማስፈጸም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፤

፮/ ሴሚናሮችን፣ ወርክሾፖችን፣ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ኮንፍረንሶችን እና ሲምፖዝየሞች ያዘጋጃል፤

፯/ በሀገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸው ሳይንሳዊ የምርምር ጆርናል፣ መጽሂቶትን እና ጋዜጦችን በማዘጋጀት በተለያዩ አማራጮች ተደራሽ ያደርጋል፤

1/ Design and provide undergraduate and postgraduate educational programs to meet the trained manpower needs of the Defense;

2/ Undertake research based on the needs of the Defense and other stakeholders by identifying research thematic areas; transfer research outputs and provide community services;

3/ Based on the needs of the Defense, design and provide professional development training;

4/ Examine and approve student admission, education quality assurance system, education program, and curriculum development activities, and student information management system for defense colleges, institutes, and academies that deliver undergraduate and postgraduate education; and provide educational credentials;

5/ Issue a comprehensive implementation directive to facilitate the implementation of the provision outlined in Sub-Article (4) of this Article;

6/ Organize seminars, workshops, national and international workshops and symposiums;

7/ Prepare nationally and internationally recognized scientific research journals, magazines, and newspapers; and avail them via a variety of channels;

፰/ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ግለሰቦች ወታደራዊና ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የምርምና ፈጠራ ሥራዎቻቸውን የሚያበለጽጉባቸው ማዕከላትን ማቋቋም፣ የፈጠራ ሥራዎቻቸውን ያደራጃል፣ ያላምዳል፣ ያስተዳድራል፤

፱/ የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲው እና ለሀገር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ላበረከቱ ሰዎች የሜዳሊያ ሽልማትና የአካዳሚክ ማዕረግ ይሰጣል፤

፲/ ኮሌጆችን፣ ኢንስቲቲዩቶችን፣ ማዕከሎችን፤ ትምህርት ቤቶችን ፤የጤና ተቋማትን፣ አካዳሚዎችን፤ የስልጠና እና የምርምር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ያቋቁማል፣

፲፩/ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እና ለአካባቢው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን ያቋቁማል፤

፲፪/ ለዩኒቨርሲቲው ከተቀመጡለት ሥልጣንና ኃላፊነቶች፣ እንደ ሁኔታው በስሩ ለሚገኙ ኮሌጆች፣ ኢንስቲትዩቶች፣ ትምህርት ቤቶች ውክልና ይሰጣል፤

፲፫/ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት በትብብር ይሰራል፤

፲፬/ በዩኒቨርሲቲው ህብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲጎለብት፤ የማንነት፣ የባህልና የታሪክ ብዝኃነትን ያረጋገጠ የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት እንዲኖር ይሰራል፤

፲፭/ ሀብት የሚያመነጩ ተቋማትን እና ኢንተርፕራይዞችን ያቋቁማል ያስተዳድራል፤

፲፮/ ተልዕኮውን ለማሳካትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚያስችል የተሟላ ተቋማዊ ቁመና እንዲኖረው የሚያደርጉ አደረጃጀቶችን መፍጠርና መሰረተ ልማቶችንና ስርዓቶችን ይዘረጋል፤

8/ Establish centers that will enrich the research and creative works of individuals with special talents, which are of military and National importance, and organize, adapt, and manage their creative works;

9/ Confer academic certificates, diplomas, and degrees as well as medals, prizes, and titles for excellence and meritorious contributions to the University or the Nation.

10/ Establish Colleges, Institutes, Centers, schools, health centers, academics, and other institutions that provide training and research services;

11/ Establish regular schools to prepare students who will join the university and provide community services;

12/ Delegate, as appropriate, its powers and responsibilities to the colleges, institutes, and schools established under it;

13/ Establish relations and work collaboratively with domestic and foreign institutions;

14/ To strengthen the national unity of the university society; strive to have a higher education service that ensures the diversity of identity, culture, and history;

15/ Establish and administer income-generating institutions and enterprises;

16/ Establish institutional setups that will enable it to achieve its mission and create good governance; and establish infrastructure and systems;

፲፯/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤

፲፰/ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

፲፱/ ለሚሰጠዉ አገልግሎት ተገቢዉን ክፍያ ያስከፍላል፤

፳/ ለመከላከያ አገልግሎት ተፈላጊ የሆኑ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚሠጡ ወታደራዊ ሙያዎችን ደረጃ ለመወሰን የሚያግዙ መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤ ይተገብራል፤

፳፩/ የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ዩኒቨርሲቲው የፖሊሲና የሥራ አስፈጻሚ አካላት

### ፮. ስለ ዩኒቨርሲቲው ቦርድ መቋቋም

፩/ በሚኒስቴሩ የሚሰየም ሰብሳቢዉን ጨምሮ ከሰባት እስከ አስራ ሦስት አባላት ሊኖሩት የሚችል የዩኒቨርሲቲው ቦርድ (ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ቦርዱ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫/ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፬/ የቦርድ አባል ሆኖ የሚሾመው ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚና ባለድርሻ አካል ተወካይ የሆነ እና በኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያለ ወይም ያገለገለ፤

ለ) በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በማስተማር ወይም በምርምር ያገለገለ ወይም እያገለገለ ያለ፤

ሐ) በግል ስብዕናው የተመሰገነ፤

17/ Own property;

18/ Enter into contracts, to sue and be sued in its own name;

19/ Charge appropriate fee for the service it provides;

20/ Develop guidelines and standards that help to determine the level of military skills that are required nationally and internationally;

21/ Carry out such other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

## PART TWO

## THE UNIVERSITY POLICY AND EXECUTIVE BODIES

### 6. Establishment of the University Board

1/ The University Board which may have Seven to Thirteen members, including the chairman assigned by the Minister (hereinafter referred to as the “Board”)is hereby established by y this Regulation.

2/ The Board shall have its own Secretary.

3/ The Board shall be accountable to the Minister.

4/ A person to be appointed as a member of the board shall fulfil the following criteria:

a) Representative of customers of the products and services of the University and representatives of stakeholders; and in positions of responsibility in the past or present;

b) Serving or had served in teaching or research works for higher educational institutions;

c) Praised for his integrity;

መ) የመከላከያን ተልዕኮዎች በማሳካትና በማኅበራዊ አገልግሎት ተሞክሮ ያለው፤

ሠ) በእውቀቱ በልምዱና በአትኩሮቱ ለከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች በአጠቃላይና ለኢትዮጵያ መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮዎች መሳካት በተለይ አስተዋጽኦ ለማበርከት ጽኑ ፍላጎት ያለው፤

፭/ የቦርድ ስብሰባዎች፣ ምልዓተ ጉባኤ፣ የውሳኔ አሰጣጥ እና የአባልነት መቋረጥ በአዋጁ አንቀጽ ፵፮፣ ፵፯ እና ፵፰ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

፮/ ቦርዱ በራሱ ውሳኔ ከሚያየው ጉዳይ ጋር ቅርበት ያለውን ሰው በአስረጂነት በስብሰባው ላይ ያለድምፅ ሊያሳትፍ ይችላል፡፡

፯. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ዩኒቨርሲቲው በትምህርት፣ በምርምርና በማማከር አገልግሎት አሰጣጥ የሚመራባቸውን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና የውስጥ መተዳደሪያ ደንቦችን ያወጣል፤

፪/ የዩኒቨርሲቲውን አደረጃጀት በመመርመር ለሚኒስትሩ በማቅረብ ያስወስናል፤

፫/ የፕሮፌሰር ማዕረግ ያጸድቃል፤

፬/ የዩኒቨርሲቲውን ስትራቴጂካዊና ዓመታዊ ዕቅዶችን የጽደቅ፣ በጀቱንም ለሚመለከተው የመንግሥት አካል አቅርቦ ያስጸድቃል፤

፭/ ዩኒቨርሲቲው ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ተቋማት ጋር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የምርምር ስራዎችን እንዲያካሂድ ያመቻቻል፤

d) Having experience in achieving the mission of defense and social services;

e) Having a special commitment to contribute with his knowledge, experience, and special focus to the achievement of the objectives of higher education in general and the mission of the University in particular.

5/ Board Meetings, Quorum, Decision making procedures and Termination of Board membership are governed by Articles of 46, 47 and 48 of the Proclamation.

6/ The board at its discretion may invite any resource person without a vote to any of its meetings.

7. **<u>Powers and Duties of the Board</u>**

The board shall have the following powers and duties:

1/ Issue general policies and internal Regulations that the University shall be guided on education, research and consultancy service provision;

2/ Examine the organizational structure of the University, and submit for decision;

3/ Approve the ranks of Professor;

4/ Approve the strategic and annual plans of the University, present and make the budget approved by the concerned government body;

5/ Facilitates the university to carry out highly important research activities with National and Foreign institutions;

፮/ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን የውስጥ አስተዳደር መመሪያ ያወጣል፣

፯/ ዩኒቨርሲቲው ከሀገር ዉስጥ እና ከዉጪ ተቋማት ጋር የሚያደርገውን ስምምነት ያጸድቃል፣

፰/ የዩኒቨርሲቲው ውሳኔ አሰጣጥና ቅሬታ አፈታት የተቀላጠፈ እና ፈጣን የአሰራር ስርዓት ያለዉ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፱/ ዩኒቨርሲቲው በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

፲/ የዩኒቨርሲቲውን የገቢ ምንጭ በተመለከተ አጠቃላይ አቅጣጫዎችን ይነድፋል፣

፲፩/ ዩኒቨርሲቲው የሚያስከፍላቸውን ክፍያዎች መንግሥት ባጸደቀው መመሪያ መሰረት ይወስናል፣

፲፪/ የራሱን የውስጥ አሰራር ደንብ ያዘጋጃል፣

፲፫/ የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፰. <u>የዩኒቨርሲቲው ሴኔት መቋቋም</u>

፩/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ተቋቁሟል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት---------ሰብሳቢ፣

ለ) የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች------------------------------------------------------------አባል፣

ሐ) የኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር------------አባል፣

መ) የኮሌጅ ዲኖች---------------------------------------------------------------------------------------አባል፣

ሠ) የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር-----------------------------------------------------አባል፣

6/ Issue internal administrative Directive that determines management and conditions of employment for academic staff of the University;

7/ Approve the University agreements concluded with national and foreign institutions;

8/ Make sure that the University has an adequate institutional system to expeditiously receive and redress grievances;

9/ Examine and give final decision on decisions passed by the University;

10/ Formulate general directions regarding the University's source of income;

11/ Determine fees to be charged by the University in accordance with Directives approved by the Government;

12/ Prepare its own internal Regulations;

13/ Perform such other activities as may be necessary for the attainment of the objectives of the University,

## 8. <u>Establishment of the University Senate</u>

1/ There is hereby established the Senate of the University having the following members:

a) University President------Chairperson;

b) Vice Presidents of the University-------------------------------------------Members;

c) College Executive Director ------------------------------------------Members;

d) College Deans ------------------------------------------------------------Member;

e) Institute Executive Director -------------------------------------------Member;

ረ) የትምህርት ጥራትና አግባብነት ዳይሬክተር-------------------------------አባል፤

ሰ) የአይሲቲ ልማት ዳይሬክተር -------------------------------------------------------------አባል፤

ሸ) የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክተር -----------------------------አባል፤

ቀ) የዩኒቨርሲቲው ሬጂስትራርና አሉሚናይ ጽ/ቤት ሃላፊ-----------------------------አባል፤

በ) ለአካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆኑ ዳይሬክተሮች---------------------አባል፤

ተ) ለምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆኑ ዳይሬክተሮች---------------------------------------------አባል፤

ቸ) የተማሪዎች ጉዳይ ዳይሬክተር-----------------------------------------------------------አባል፤

ኀ) የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቡድን ----------------------------------------------------አባል፤

ነ) የመምህራን ሦስት ተወካዮች -----------------------------------------------------------አባል፤

ኘ) የተማሪዎች ካውንስል ተወካይ -------------------------------------------------------アባል፤

አ) የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዝዳንት ፅ/ቤት ኃላፊ -------------------------------------------አባል፡፡

፪/ ሴኔቱ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫/ ሴኔቱ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡፡

፱. <u>የሴኔቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ የትምህርት፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እና የአስተዳደር ጉዳዮችን የሚመለከቱ የአፈጻጸም መመሪያዎችን ያወጣል፤

f) Education Relevance and Quality Assurance Director------------Member;

g) ICT development Director---------------------------------------------Member;

h) Public and International Relations Director-------------------------Member;

i) University Registrar and Alumni Affairs Director----------------Member;

j) Directors accountable for the Academic Vice President----Member;

k) Directors accountable for the Research and Technology Transfer Vice President-----------------Member;

l) Students' Affairs Director--------------------------------------------------Member;

m) Women, and Social Affairs Team ---------------------------------Member;

n) Three Representatives of Teachers-------------------------------------Member;

o) Representative of Students' Council -----------------------------------Member;

p) University President Office Head ----------------------------------Member.

2/ The Senate shall have its own Secretary.

3/ The Senate shall be accountable to the Board.

9. **<u>Powers and Duties of the Senate</u>**

1/ Issue implementation Directives on education, research, community service and administrative issues;

፪/ ዩኒቨርሲቲው የሚሰጣቸውን የትምህርት መርሐ-ግብሮች፣ ስርዓተ ትምህርቶች፣ የምርምር ፕሮጀክቶችና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ጥራታቸው የተረጋገጠና ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃቸዉን የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

፫/ የዩኒቨርሲቲውን የትምህርት ካሌንደር መርምሮ ያጸድቃል፤

፬/ የሙሉ ፕሮፌሰር ማዕረግ ዕድገት ጥያቄዎችን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለቦርዱ ያቀርባል፤

፭/ የተባባሪ ፕሮፌሰርና የረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ ዕድገት ጥያቄን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፮/ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት ለሀገርና ለመከላከያ ልዩ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ግለሰቦች የክብር ዲግሪና ሌሎች ሽልማቶች እንዲሰጥ መርምሮ ያጸድቃል፤

፯/ የተማሪዎች ቅበላ መስፈርቶችን፣ ከትምህርት ማቋረጥና እንደገና ቅበላ መመዘኛዎችን እና አጠቃላይ የአፈጻጸም ስርዓቶችን ያወጣል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፤

፰/ ዲግሪዎችን፣ ዲፕሎማዎችን፣ የምስክር ወረቀቶችን፣ የተለያዩ ሽልማቶችን እና አካዳሚክ ማዕረጎች የሚሰጥበትን መስፈርቶች ይወስናል፤

፱/ አጠቃላይ የፈተና አሰጣጥ አቅጣጫዎችን ይወስናል፤

፲/ የመካለከያን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ አዳዲስ የትምህርት ፕሮግራሞች እና የምርምር ማዕከላት እንዲከፈቱ ወይም እንዲታጠፉ ወይም እንዲዋሃዱ ጥያቄ ሲቀርብለት መርምሮ ያጸድቃል፤

2/ Monitor and ensure that educational programs, curriculums, research projects, and community service activities are of the highest quality and in compliance with national and international standards;

3/ Approve the academic calendar of the University;

4/ Propose promotion of professorship to the Board;

5/ Approve academic promotion of Associate professor and Assistant Professor;

6/ Up on the recommendation of the University President, approves awards of honorary degrees and other prizes to individuals who contributed outstanding achievements for the country and the defense;

7/ Set criteria and general implementation systems for admission, withdrawal, and re-admission of students; and monitor its implementation;

8/ Determine the criteria to be used for conferring degrees, diplomas, academic certificates, other different prizes and academic awards;

9/ Decide general directions for exam provision;

10/ Examine and approve requests on the opening, closing, or merging of academic programs and research centers based on the interest of the defense;

፲፩/ የዩኒቨርሲቲውን ወይም ዩኒቨርሲቲው ድጋፍና ክትትል ለሚያደርግላቸው የመከላከያ ኮሌጆች እና አካዳሚዎች ተመራቂ ተማሪዎች ዝርዝር፣ ብቁነትና አግባብነት መርምሮ ያጸድቃል፤

፲፪/ በሴሚሰተር ቢያንስ አንድ ጊዜ ሰብሰባዎችን ያካሂዳል፤

፲፫/ ሌሎች የሴኔቱን ውሳኔ በሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲፬/ በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

**፲. <u>የዩኒቨርሲቲው አመራር ካውንስል ስለማቋቋም</u>**

፩/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲው አመራር ካውንስል ተቋቁሟል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት-------------------------------------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች ------------------------------------------አባል፤

ሐ) የኮሌጅ እና የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ----------------------------አባል፤

መ) የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ፅሕፈት ቤት ኃላፊ-----------------------------------አባል፡፡

፪/ የአመራር ካውንስሉ ተጠሪነት ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡

**፲፩. <u>የዩኒቨርሲቲዉ አመራር ካውንስል ሥልጣንና ተግባር</u>**

የዩኒቨርሲቲው አመራር ካውንስል የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

11/ Examine and approve the list, illegibility, and relevance of the University graduating students or graduating students of Defense College or Academy students supported and supervised by the University;

12/ Conduct meetings at least Once per semester;

13/ Decide on other matters which require the decision of the Senate;

14/ Perform such other activities assigned by the board.

**10. <u>Establishment of the University Management Council</u>**

1/ There is hereby established a Management Council having the following members:-

a) The University President-------------------------------------------Chairperson;

b) The University Vice Presidents ---------------------------------------Member;

c) College and Institute Executive Directors ---------------------Member;

d) The University President Office Head--------------------------Member.

2/ The Management Council shall be accountable to the University President.

**11. <u>Powers and Duties of the University Management Council</u>**

The University Management Council shall have the following powers and duties:

፩/ የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ መሰረት ያደረገ የረጅም ጊዜና የአጭር ጊዜ ዕቅድ ያወጣል፣ በጀት ያዘጋጃል፣ ለቦርዱ እና ለሚመለከታቸዉ የመንግሥት አካላት በማቅረብና በማጸደቅ ሥራዎች በእቅዱ መሰረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

፪/ ተማሪውና ስታፍ ሠራተኛው በሙያ እና በወታደራዊ ሥነ-ምግባር የታነጸ እንዲሆን የሥነ-ልቦና ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፤

፫/ ትምህርት፤ ምርምር እና ስልጠናዎች ከመከላከያ ተጨባጭ ፍላጎት እና ከሰራዊቱ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዕድገት ጋር መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፤

፬/ የቦርዱን እና የሴኔቱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤

፭/ የመከላከያና የዩኒቨርሲቲው ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲከበሩ እና እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፮/ የጥናት፣ የምርምርና የፈጠራ ሥራዎችን በስፋትና በጥራት ለማካሄድ መምህራን እና ተመራማሪዎች በጋራና በግል እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ አመቺ ሁኔታም ይፈጥራል፤

፯/ አዲስ ለሚገቡ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የሚቀመጡ መመዘኛዎች እንደ አስፈላጊነቱ ይመረምራል፣ ያሻሽላል፤

፰/ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚቀርበውን የበጀት ድልድል ፍትሃዊነት በማየት ያጸድቃል፤ የአፈጻጸም ስርዓቱንም ገምግሞ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

፱/ ዩኒቨርሲቲው ከመሰል ተቋማት ጋር የሚያደርገውን የግንኙነት ስርዓት ያበጃል፣ ይወስናል፤

1/ Based on the objectives of the University, prepare short and long-term plan and budget; approve by the board and concerned government bodies and ensure that activities are carried out according to the plan;

2/ Ensure that students and academic staff are built with professionalism and military ethics;

3/ Ensure that the education, research, and training are aligned with the concrete needs of the defense and the advancement of the use of technology by the military;

4/ Implement decisions of the board and the Senate;

5/ Ensures that the policies, rules, and guidelines of the defense and the university are respected and implemented;

6/ Create conducive conditions and encourage the teaching staff and researchers to engage largely and effectively in research and innovation activities in groups and individually;

7/ Evaluate and improve admission requirements, as appropriate, for newly admitted students of the University;

8/ Evaluate, monitor, and supervise the fairness of the University budget allocation by the president and implementation system;

9/ Establish, determine a system for the University's relation with similar institutions;

፲/ ዩኒቨርሲቲው በአወቃቀር፣ በሰው ኃይልና በአሰራር ብቃቱን እያረጋገጠ እንዲሄድ ቀጣይ ጥረት ያደርጋል፤

፲፩/ ሌሎች በሴኔቱና በቦርዱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፪. የዩኒቨርሲቲው አመራር አካላት ሹመትና ተጠሪነት**

፩/ ዩኒቨርሲቲው አንድ ፕሬዝዳንትና ቁጥራቸዉ እንደ አስፈላጊነቱ የሚወሰን ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይኖሩታል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት በመከላከያ ሰራዊት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ መሰረት የሚሾም ሆኖ፣ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

፫/ የምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ የኮሌጅ እና የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ምደባ መስፈርትንና ውድድርን መሰረት በማድረግ በመከላከያ ሰራዊት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ መሰረት የሚፈጸም ሲሆን ተጠሪነታቸው ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡

፬/ የዲኖች እና የዳይሬክተሮች ምደባ ውድድርን መሠረት ባደረገ መልኩ በመከላከያ ሠራዊት መተዳደሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፷/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ለ) ድንጋጌ መሠረት ይፈጸማል፡፡

10/ Continuously strive to ensure effectiveness on institutional set-up, human resource, and procedure of the University;

11/ Carry out such other activities given by the Senate and the board.

**12. Appointment and Accountability of the University Leadership**

1/ The University shall have a President and other vice-Presidents as appropriate.

2/ The University President shall be appointed as per Paragraph (a) of Sub-Article (2) of Article 21 of the Defense Forces Administration Council of Ministers Regulation No. 460/2019, and is accountable to the Minister.

3/ The Vice-Presidents of the University, College, and Institute Executive Directors shall be selected on merit and competitive bases, and appointed as per Paragraph (b) of Sub-Article (2) of Article 21 of the Defense Forces Administration Council of Ministers Regulation No. 460/2019, and are accountable to the University President.

4/ Deans and Directors shall be selected on merit and competitive bases, and appointed as per Paragraph (b) of Sub-Article (2) of Article 21 of the Defense Forces Administration Council of Ministers Regulation No. 460/2019.

፭/ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት አንድ የሥልጣን ዘመን ፮ (ስድስት) ዓመት ሆኖ ለሁለት የሥልጣን ዘመን ሊያገለግል ይችላል፡፡

፮/ የዩኒቨርሲቲው የምክትል ፕሬዚዳንት፣ የኮሌጅ እና ኢንስቲቲዩት ዋና ዳይሬክትር አንድ የሥልጣን ዘመን ፬ (አራት) ዓመት ሆኖ ለሁለት የሥልጣን ዘመን ሊያገለግል ይችላል፡፡

፯/ የዲን ወይም የዳይሬክተር አንድ የሥልጣን ዘመን ፪ (ሁለት) ዓመት ሆኖ ለሁለት የሥልጣን ዘመን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## ፲፫. <u>የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የዩኒቨርሲቲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የዩኒቨርሲቲውን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪/ የዩኒቨርሲቲውን የሥራ ዕቅድ ያወጣል ሲጸድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፫/ የዩኒቨርሲቲውን የሥራ ዕቅድና ፕሮግራም በጀት በማዘጋጀት ለቦርድ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፰) ድንጋጌ መሰረት ለኮሌጆች፣ ለኢንስቲትዩት እና በስሩ ላሉ ሌሎች የሥራ ክፍሎች በጀት ይመድባል የተመደበውን በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

5/ The university president may hold office for two terms, with each term lasting 6 (Six) years.

6/ The vice president of the university, and the Executive Directors of colleges and institutes may hold office for Two terms, with each term lasting 4 (Four) years.

7/ The university dean or director may hold office for Two terms, with each term lasting 2 (Two) years.

## 13. <u>Powers and Duties of the University President</u>

The University President shall be the Chief Executive of the University and shall have the following powers and duties:

1/ Direct, administer, and supervise the overall activities of the University;

2/ Prepare the activity plan of the University, implement it when approved, and follow up its implementation;

3/ Prepare and submit the activity plan and program budget of the University to the board; and implement when approved;

4/ Allocate budget for colleges, institutes, and other working units; monitor and control the proper use of the allocated budget as per Sub-Srticle (3) of this Article and Sub-Article (8) of Article 11;

፭/ በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ የትምህርት መርሐ-ግብሮች እና የጥናትና ምርምር ሥራዎች የተቋሙን ችግሮች የሚፈቱ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

፮/ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና የሰራዊት አባላት የሚሊተሪ ሳይንስና ጥበብ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር፣ የአካልና የሥነ-ልቦና ዝግጁነታቸው እንዲረጋገጥ በቅርብ ይከታተላል፣ እነዚህን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ይፈጥራል፣ አመራር ይሰጣል፤

፯/ የዩኒቨርሲቲውን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለሚኒስትሩ እና ለቦርዱ ያቀርባል፤

፰/ የዩኒቨርሲቲውን ንብረት በመንግሥት መመሪያ መሰረት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፱/ ዩኒቨርሲቲው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪና በቴክኖሎጂ የዳበረ ጠንካራ ተቋም እንዲሆን ይሰራል፤

፲/ የመከላከያና የዩኒቨርሲቲው ደንቦች፣ መመሪያዎችና የፕሮፌሽናል ሰራዊት ግንባታ ሥራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩/ በዩኒቨርሲቲው ስም የሚደረጉ ማናቸውንም ስምምነቶች እና ሰነዶች ይፈርማል፤

፲፪/ በዩኒቨርሲቲው ስም የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትና እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤

፲፫/ ከሚኒስቴሩ ወይም ከቦሩዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

5/ Follow up and ensure that educational programs offered by the University and research activities solve the problems of the institution;

6/ Lead and closely monitor the university students and army members to increase their understanding of military science and art, and ensure their physical and psychological readiness; create an organization to carry out these tasks;

7/ Evaluate the performance of the University and submit updated reports to the ministry and the Board;

8/ Administer and manage properties of the University in accordance with government Directives;

9/ Strive to make the University an internationally competitive and technologically strong institution;

10/ Ensure that the defense and University Regulations, Directives, and professional army-building activities are properly implemented;

11/ Sign any agreements and documents concluded on behalf of the University;

12/ Open and operate a bank account in the name of the University;

13/ Carry out such other activities given by the Board or the Ministry.

## ፲፬. <u>የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የአካዳሚክ ሥራውን በበላይነት ይመራል፣ የአካዳሚክ ዲኖች ካውንስልን ይሰበስባል፤

፪/ የዩኒቨርሲቲው ስርዓተ-ትምህርት ደረጃ መጠበቁን ያረጋግጣል፣ የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ ጥራት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

፫/ የአካዳሚክ ሠራተኞች ሙያቸውን ለማሳደግ የሚያስችል የሰው ሀብት ልማት ስርዓትን ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፬/ የመምህራን ውል ማደስንና የደረጃ ዕድገትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን እየመረመረ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣ ዩኒቨርሲቲውን ወክሎ የመምህራንን ቅጥር ይፈርማል፤

፭/ አዳዲስ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች እንዲጀመሩ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነቱንም ይቆጣጠራል፤

፮/ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ሥራዎች የሚመሩበትን መመሪያዎችና ጋይድላይኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያስጸድቃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፯/ ለመማር ማስተማር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መሟላታቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

## 14. <u>Powers and Duties of the Academic Vice-President of the University</u>

The Academic Vice-President of the University shall be accountable to the University President and shall have the following powers and duties:

1/ Lead the academic work as a head, and chair the meeting of the Dean's Council;

2/ Ensure that the standards of the curriculum of the University are maintained; recommend for improvement; and ensure the quality of the teaching-learning process;

3/ Design a human resource development system for the professional development of academic staff; and follow up on its implementation;

4/ Evaluate requests submitted for renewal of teaching staff contracts and promotion, and forward recommendations to the concerned body; sign teaching staff employment contracts on behalf of the University;

5/ Ensure that studies for the commencement of new academic programs are conducted, and supervise their implementation;

6/ Ensure the preparation of Directives and guidelines that guide the academic activities of the university, and monitor their implementation.

7/ Follow up and ensure the availability of inputs required for teaching and learning;

፰/ የአካዳሚክ ፕሮግራሞች ዝግጅትና አቅርቦት፣ የበጀት ፍላጎትና አፈጻጸም እና የሰው ኃይል ፍላጎትን በተመለከተ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ሪፖርት ያቀርባል፤

፱/ የዩኒቨርሲቲውን የአካዳሚክ ሥራ አፈጻጸም ግምገማዎችን ያደርጋል፣ ሪፖርቶችን አጠናቅሮ ለፕሬዝዳንቱ ያቀርባል፤

፲/ በዩኒቨርሲቲው ዋና መስሪያ ቤትና በኮሌጆች ያሉ የአካዳሚክ ዘርፍ ክፍሎችን ትስስር ስርዓት ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲፩/ በአካዳሚክ ጉዳዮች ላይ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንት ያማክራል፤

፲፪/ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፭. <u>የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባር</u>**

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የዩኒቨርሲቲውን የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ካውንስልን ይሰበስባል፤

፪/ የዩኒቨርሲቲው ጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚመሩበትና የሚተገበሩበት የጥናትና ምርምር መመሪያዎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች፣ የጥራት ደረጃ መከታተያ ስታንዳርዶች እንዲነደፉ በሚመለከታቸው አካላት እንዲጸድቁ ያደርጋል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውንም ይከታተላል፤

8/ Submit reports to the University President regarding the preparation and provision of academic programs, budget needs and utilization, and human resource needs;

9/ Evaluate the academic performance of the University, compile reports, and submit them to the President;

10/ Design a linkage system between the University head office and the college academic sector departments, follow up on its implementation;

11/ Advise the University President on academic matters;

12/ Carry out such other activities given by the University President.

**15. <u>Powers and Duties of Research and Technology transfer Vice-President</u>**

The University Research and Technology transfer Vice-president shall be accountable to the University President and shall have the following powers and duties:

1/ Lead the University research, technology transfer, and community service activities; and convenes research and technology transfer council;

2/ Ensure that research policies, Directives, procedures, and quality monitoring standards that guide the implementation of research activities of the University are prepared and approved by concerned organs; and follow its implementation;

፫/ የዩኒቨርሲቲውን የጥናትና ምርምር ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

3/ Prepare research strategic plan of the University; and follow its implementation;

፬/ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች በተደራጀና ውጤታማ በሆነ መልክ እንዲሰሩ ትኩረት በማድረግ ይሰራል፤

4/ Ensure that technology transfer activities are implemented in an organized and efficient manner;

፭/ የዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር ውጤቶች የሚቀርቡባቸው ኮንፈረንሶች፣ ወርክሾፖች እና ሲምፖዚየሞችን ያዘጋጃል፣ የምርምር ጆርናሎችም እንዲቋቋሙና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

5/ Organize conferences, workshops, and symposiums to present the results of the University's research works; establish and distribute research Journals;

፮/ የዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር ሥራዎች ጥራትና ደረጃ በቀጣይነት ለማሻሻል ጥናት ያካሂዳል፣ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤

6/ Research to continuously improve the quality and standard of research activities of the University; and ensure their implementation;

፯/ በዩኒቨርሲቲው ስር የመከላከያን ተልዕኮና ስኬት በከፍተኛ ደረጃ የሚያጎለብቱ የምርምርና ስርፀት ሥራዎች የሚሰሩባቸው የምርምር ተቋማት በጥናት ላይ ተመስርተው እንዲደራጁ ይሰራል፤

7/ Based on research, strive to establish research institutions under the University that work on research and dissemination activities that can greatly enhance the mission and success of the defense;

፰/ ከመከላከያ የተለያዩ ክፍሎች፣ ከሌሎች የሀገር ውስጥና የውጪ ሀገር ተቋማት ጋር በትብብር የሚሠሩ የምርምር ሥራዎች በአግባቡ እንዲመሩ የጋራ ዕቅዶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፤

8/ Prepare joint plans for the proper management of research activities that are conducted in collaboration with various sections of the defense, and other local and international institutions; and monitor their implementation;

፱/ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን በተቀላጠፈና ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈጸምና ለመተግበር የሚያግዝ መመርያ በማዘጋጀት ያስጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይመራል፤

9/ Develop and approve a Directive that helps to implement consultancy and community service activities efficiently and effectively; and lead its implementation;

፲/ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳዮች ላይ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንት ያማክራል፤

10/ Advice the University President on research and technology transfer matters;

፲፩/ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፮. <u>የአስተዳደር እና የተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር እና የተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የዜግነትና የሙያ ግዴታውን በጠንካራ እምነትና ፍላጎት እየተወጣ የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮ በብቃት እንዲያሳካ አመራር ይሰጣል፣ የቅርብ ድጋፍ ያደርጋል፤

፪/ የመከላከያ እና የዩኒቨርሲቲው ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲታወቁና እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፫/ የዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል ፍላጎት መንግሥት ባጸደቀው አቋም መሰረት መሟላቱን ያረጋግጣል፣ የሰራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ ስንብትና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች በሕግ አግባብ መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣ ሰራተኞች መብታቸው ተከብሮላቸው ግዴታቸውን እንዲወጡ ሕግን ተከትሎ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፤

፬/ የዩኒቨርሲቲው እና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጸጥታና ደህንነት እንዲሁም ንብረት የሚያስጠብቅ ስርዓት እንዲኖርና እንዲጎለብት ተገቢውን አመራር ይሰጣል፤

11/ Carry out such other activities given by the University President.

**16. <u>Powers and Duties of the Administrative and Students Affairs Vice President</u>**

The University Administrative and Students Affairs Vice President shall be accountable to the University President and shall have the following powers and duties:

1/ Provide leadership to help the University's community discharge their citizenship and professional obligations with strong belief and interest in order to achieve the University's missions; and provide close support;

2/ Make sure that the defense and University Policies, Regulations, and Directives are known and implemented by the University community;

3/ Ensure that the University's human resource needs are fulfilled as per the institutional arrangement approved by the Government; supervise and guide the recruitment, transfer, and dismissal of staff, and other administrative matters are performed as per the law; take the necessary measure in accordance with the law to ensure that rights of the employees are respected in order to enable them to discharge their responsibilities;

4/ Provide appropriate leadership to create and strengthen a security system that protects the security and safety as well as property of the University and University community;

፭/ የመማር ማስተማር፣ የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና ማህበረሰብ አገልግሎት ሂደቶችን የሚደግፍ የማቴሪያል አቅርቦት መኖሩን ያረጋግጣል፣

፮/ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚያስፈልጉ የጤና፣ የተማሪዎች ምግብ፣ የትራንስፖርት ድጋፍ እና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤

፯/ በአስተዳደርና በተማሪ ኑሮ ጉዳዮች ላይ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንት ያማክራል፤

፰/ የአስተዳደርና የግብዓት አቅርቦት ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ የዘርፉን የሥራ አፈጻጸም ወቅታዊ ግምገማዎች ያካሂዳል፤ ሪፖርት ያቀርባል፤

፱/ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፯. <u>ስለተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ምክትል ፕሬዝዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ የዩኒቨርሲቲውን የፋይናንስ አቅም የሚያሳድጉ የገቢ ማመንጫ ድርጅቶችና የቢዝነስ አማራጮችን አቅርቦ ያጸድቃል፣ ፕሮጀክቶችን ይቀርጻል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፤

፪/ የካምፓስ ህንፃዎችን ግንባታ፣ እንክብካቤ፣ ልማትና ዕድገት ይከታተላል፤

፫/ የዩኒቨርሲቲውን የመጽህፍት እና ጆርናል ህትመት ማዕከል ያደራጃል፣ የህትመት ሥራዎችን ያከናውናል፣ የህትመት ውጤቶች ሽያጭ ማዕከል ያቋቁማል፤

5/ Ensure the availability of material that supports the teaching-learning, research, and technology transfer processes;

6/ Ensure that health, student food, transport, and other necessary services are fulfilled for the University society;

7/ Advice the University President on administrative and student livelihood matters;

8/ Prepare and submit budget and plan of administration and input supply; timely evaluate the performance evaluation of the sector; and submit report thereof;

9/ Carry out such other activities as may be assigned to him by the University President.

**17. <u>Powers and duties of Organizational Development and Business Vice President</u>**

1/ Propose and approve income-generating organizations and business options that increase the university's financial capacity; design, expand, and manage projects;

2/ Monitors the construction, maintenance, development, and growth of campus buildings;

3/ Establish the university’s book and journal publishing center; perform printing; and establish a sales center for print products;

፬/ በዩኒቨርሲቲው ደህንነቱ የተጠበቀ፤ ጠንካራ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል እንዲቋቋምና ዓለም አቀፋዊ ትስስር እንዲኖረው ይሰራል፣ ክትትል ያደርጋል፤

፭/ የተለያዩ ሶፍትዌሮችን በመቅረጽና በማበልጸግ ለዩኒቨርሲቲውና ሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት ያቀርባል፤

፮/ ከአካዳሚክ እና ከምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዝዳንቶች ጋር በመቀናጀት የዩኒቨርሲቲውን ገቢ የሚያሳድጉ ሥራዎችን ይሰራል፤

፯/ ሕግ በሚፈቅደው መሰረት የንግድ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም እንዲተገበሩ ይሰራል፤

፰/ በዩኒቨርሲቲው ለትርፍ የሚቋቋሙ ሆቴሎችን፣ ሱፐርማርኬቶችን፤ የመዝናኛ ማዕከሎችን በኃላፊነት ያደራጃል፤ ይመራል፤

፱/ ከገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች እና ኢንተርፕራይዞች የሚገኝ ገቢን ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፤

፲/ ከሚያገኘው ገቢ ፕሬዝዳንቱን በማስፈቀድ የመሰረተ-ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን እየቀረጸ ይተገብራል፤

፲፩/ የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ሥራዎችን በተመለከተ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዝዳንት ያማክራል፤

፲፪/ ሌሎች በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

4/ Establish a strong and secure information communication technology center; and work towards having international connections;

5/ Develop various software and provide them to the university and other governmental and non-governmental organizations;

6/ Strive to increase the income of the university in collaboration with the vice presidents of academic, and research and community services;

7/ Establish and operate business enterprises as per by law;

8/ Establish and responsibly lead hotels, supermarkets, and recreation centers for-profit at the university;

9/ Monitor and manage income generated from income-generating projects and enterprises;

10/ Design and implement infrastructure expansion projects from the income it earns with the approval of the president;

11/ Advise the University President on institutional development and business matters.

12/ Carry out such other activities as may be assigned to him by the University President.

**፲፰. ስለ ዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ዲኖች ካውንስል መቋቋም**

፩/ በዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት እና በኮሌጆች እና ትምህርት ቤቶች አካዳሚክ ዲኖች መካከል የሥራ ትስስርን ለማሳለጥ የሚከተሉትን አባላት የያዘ የአካዳሚክ ዲኖች ካውንስል ተቋቁሟል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ምክትል ፕሬዝዳንት-------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) የኮሌጅ እና የትምህርት ቤት አካዳሚክ ዲኖች ---------------------------------አባል፤

ሐ) ለአካዳሚክ ም/ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆኑ ዳይሬክተሮች-------------------------አባል፤

መ) የትምህርት ጥራትና አግባብነት ዳይሬክተር--------------------------አባል፡፡

፪/ ካውንስሉ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫/ ካውንስሉ ተጠሪነቱ ለሴኔቱ ይሆናል፡፡

፬/ ካውንስሉ ቢያንስ በየወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

**፲፱. የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ዲኖች ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት**

የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ዲኖች ካውንስል የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ በዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ የትምህርትና ስልጠና ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

፪/ የዕቅድ አፈጻጸም ሂደቱን ቢያንስ በየወሩ ይገመግማል፤ ማስተካከያ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፤

**18. Establishment of the University Academic Dean's Council**

1/ To facilitate the working relationship between the Academic Vice-President of the University and the Academic Deans of Colleges and schools, there is hereby established the Academic Dean's Council of the University having the following members:

a) Academic Vice-President of the University--------------Chairperson;

b) Academic Deans of College and Schools--------------------Members;

c) Directors accountable for the Academic Vice-President ------------------------------------------Members;

d) Education Relevance and Quality Assurance Director--------------------------------------------------Member.

2/ The Council shall have its own Secretary.

3/ The Council shall be accountable to the Senate.

4/ The Council shall meet at least once a month.

**19. Powers and Duties of the University Academic Dean's Council**

The University Academic Dean's Council shall have the following powers and duties:

1/ Work thoughtfully on the preparation and implementation of strategic, and annual education and training plans of the University;

2/ Evaluate plan implementation at least monthly and set adjustment directions;

፫/ የትምህርትና ስልጠና ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና አሰራሮችን ያዘጋጃል ሲጸድቅለትም በትክክል መተግበራቸውን ይከታተላል፤

፬/ የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያዎችን መርምሮ ያጸድቃል፣ የፕሮግራም ለውጦችንና አዲስ የሚጀመሩ ፕሮግራሞችን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያቀርባል፤

፭/ የኦዲት ሥራዎች እንዲሰሩ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ተሠርተው ሲመጡም መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሴኔት ያቀርባል፤

፮/ ዩኒቨርሲቲው በሚመለከተው የመንግሥት አካል ኦዲት በሚደረግበት ወቅት አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ የውስጥ ግምገማ ሰነድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ የተዘጋጀውንም ሰነድ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለሴኔት ያቀርባል፤

፯/ የፈተና አሰጣጥንና የተማሪዎችን ውጤት በየሴሚስቴሩ ይመረምራል፣ የማሻሻያ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያሳውቃል፤

፰/ ለካውንስሉ ውሳኔ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ያስጠናል፤

፱/ ሌሎች በሴኔትና በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሠጡትን የአካዳሚክ ሥራዎች ያከናውናል፡፡

3/ Prepare educational and training Regulations, Directives, and procedures; and monitor their implementation when approved;

4/ Examine and approve curriculum amendments; evaluate and propose recommendations for the University Senate on program changes and opening of new programs;

5/ Provide direction for audit activities to be conducted; when it is done, examine and submit to the Senate with recommendation;

6/ Set direction when the University is audited by the concerned government body; prepare an internal evaluation document; review and submit the recommendation to the Senate;

7/ Examine procedures of examination and student results each semester, set direction for improvement, and notify the University Senate;

8/ Commission research works that are necessary for the Council's decision;

9/ Carry out such other academic activities as may be assigned to him by the Senate and University President.

**፳. ስለ ዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ካውንስል መቋቋም**

፩/ በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዝዳንት፣ በኮሌጆች የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዲኖች እና በምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱ መካከል የሥራ ትስስርን ለማሳለጥ የሚከተሉትን አባላት የያዘ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ካውንስል ተቋቁሟል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ፕሬዝዳንት--------------ሰብሳቢ፤

ለ) የኮሌጆች የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዲኖች---------------------አባል፤

ሐ) ለምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆኑ ዳይሬክተሮች ------------------------------------------አባል፤

መ) በሴኔት የሚመረጡ ሦስት ከፍተኛ ተመራማሪዎች ---------------------አባል፤

ሠ) የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተሮች--------------------------አባል፡፡

፪/ ካውንስሉ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫/ ካውንስሉ ተጠሪነቱ ለሴኔቱ ይሆናል፡፡

፬/ ካውንስሉ ቢያንስ በየወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

**20. Establishment of the University Research and Technology Transfer Council**

1/ To facilitate the working relationship between the research and technology transfer Vice-President of the University; Research and Community Service Deans of Colleges; and the Research and Development Institute, the Research and Technology Transfer Council of the University having the following members is hereby established:

a) The University Research and Technology transfer Vice-President-----------------------------Chairperson;

b) Research and community service Deans of Colleges ---------Members;

c) Directors accountable for Research and Technology transfer Vice-President--------------------Members;

d) Three Senior Researchers to be elected by the Senate---------------------------------------------------Members;

e) Directors of Research and Development Institute ------------------------------------------------Members.

2/ The Council shall have its own Secretary.

3/ The Council shall be accountable to the Senate.

4/ The Council shall meet at least Once a month.

**፳፩. <u>የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት</u>**

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ካውንስል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ በዩኒቨርሲቲው የምርምር፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የተቋማት ድጋፍ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

፪/ ቢያንስ በየወሩ የዕቅድ አፈጻጸም ሂደቱን ይከታተላል፣ ማስተካከያ አቅጣጫዎች ያስቀምጣል፤

፫/ የምርምርና ልማት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የትምህርት ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር፣ የማህበረሰብ እና የማማከር አገልግሎት ደንቦች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች በማዘጋጀት በሴኔት እንዲጸድቁ ያደርጋል፤ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፤

፬/ የዩኒቨርሲቲው የምርምር ስራዎች አቅጣጫና የምርምር ጭብጦች እንዲዘጋጁ በማድረግ ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት አቅርቦ ያስወስናል፤

፭/ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውና የተቋሙን አቅም በከፍተኛ ደረጃ ሊያጎለብቱ የሚችሉ የምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲነደፉ ያደርጋል፤ ሲቀርቡም መርምሮ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት ያቀርባል፤

**21. <u>Powers and Duties of the University Research and Technology Transfer Council</u>**

The University Research and Technology Transfer Council shall have the following powers and duties:

1/ Work mainly focusing on research, technology transfer, institutional support, community service strategic and annual plan preparation and implementation;

2/ Evaluate the plan implementation process at least monthly and set adjustment directions;

3/ Draft Regulations, Directives, and procedures for research and development, technology transfer, academic-industry linkage, community, and consultancy services; approve them by the Senate; and monitor their implementation;

4/ Set directions for research works and prepare research themes of the University; submit to the University Senate for approval;

5/ Design research programs and projects that have strategic importance and greatly enhance the capacity of the institution; examine and submit recommendations to the University Senate;

፮/ በዩኒቨርሲቲው ስር የተቋቋመውን የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት አቅም የሚያሳድጉ የሰው ኃይል፣ ፋሲሊቲ፣ መሰረተ ልማት፣ በጀት እና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶች ማሟላት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

፯/ በኮሌጆች የሚሰሩ የምርምር ስራዎችን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

፰/ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የምርምር ሲምፖዚየሞችን፣ ወርክሾፖችን እና ሴሚናሮችን ያዘጋጃል፤ አፈጻጸማቸዉን ይከታተላል፤

፱/ ደረጃቸውን የጠበቁ የምርምር መጽሄቶች እንዲዘጋጁ አቅጣጫ ይሰጣል፤ የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚ ክፍሎች ተደራሽ የሚሆኑበትን አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸማቸዉን ይከታተላል፤

፲/ ከሀገር ዉስጥና ከውጭ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ የአገልግሎት ተቋማት እና የመንግሥት ተቋማት ጋር በጋራ የሚሰሩ የምርምርና የአጋርነት ሥራዎችን በሚመለከት አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ማስተካከያዎችን ይሰጣል፤

፲፩/ ለካውንስሉ ውሳኔ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን ያስጠናል፤

፲፪/ ሌሎች በሴኔትና በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡትን የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎች ያከናውናል፡፡

6/ Work mainly focusing on issues such as, human resources, facility, infrastructure, budget, and fulfilling other necessary inputs that develop the capacity of the Research and Development Institute established under the University;

7/ Monitor and support research activities undertaken by colleges;

8/ Organize symposiums, workshops, and seminars at the university level; and monitor their implementation;

9/ Set guidance for the publication of standardized research journals and accessibility of research findings to users; and monitor its implementation;

10/ Set guidance on research and collaborative activities to be conducted jointly with universities in and outside the country, industries, service institutions, and governmental organizations; monitor its implementation; and provide corrective measures;

11/ Commission research that is necessary for the Council's decision;

12/ Carry out such other research and technology transfer activities as may be assigned to him by the Senate and University President.

**፳፪. ስለ ዩኒቨርሲቲዉ የአስተዳደርና የተማሪዎች ጉዳይ ካውንስል መቋቋም**

፩/ የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና የተማሪዎች ጉዳይ ካውንስል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ ሆኖ ተቋቁሟል፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና የተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት---------------------------------------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) ለዩኒቨርሲቲው የአስተዳደር ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆኑ ዳሬክተሮች-----------------------------------------------አባል፤

ሐ) የኮሌጅ እና የኢንስቲትዩት የአስተዳደር ዳይሬክተሮች--------------------------አባል፡፡

፪/ ካውንስሉ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫/ ካዉንስሉ ተጠሪነቱ ለሴኔት ይሆናል፡፡

፬/ ካውንስሉ የራሱን የስብሰባ ጊዜ ይወስናል፡፡

**፳፫. የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና የተማሪዎች ጉዳይ ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት**

የዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና የተማሪዎች ጉዳይ ካውንስል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩/ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎችና የሰራዊት አባላት ሕገ-መንግሥታዊ ግንዛቤያቸዉን የሚያጎለብት ሥራዎች መሰራታቸውን ይከታተላል፤

**22. Establishment of the University Administrative and Students Affairs Council**

1/ The University Administrative and Students Affairs Council there is hereby established having the following members:

a) The University Administrative and Students Affairs Vice-President--------------------------------Chairperson;

b) Directors accountable for the University Administrative Vice-President---------------------Member;

c) Administrative and Students Affairs Director of the college and institute----------------------Member.

2/ The Council shall have its own Secretary.

3/ The Council shall be accountable to the Senate.

4/ The Council shall decide its meeting schedule.

**23. Powers and Duties of the the University Administrative and Students Affairs Council**

The University Administrative and Students Affairs Council shall have the following powers and duties:-

1/ Monitor activities for developing the constitutional awareness of the University students and members of the defense;

፪/ በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ዘንድ የመከላከያ ቁልፍ እሴቶችና ተቋማዊ ባህሎችን የመገንባት ሥራ መሰራታቸውን ይከታተላል፤ ግድፈቶች ሲታዩ ማስተካከያዎችን በማድረግ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ሪፖርት ያደርጋል፤

፫/ የዩኒቨርሲቲውን የአስተዳደር ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ያስጸድቃል፤ መተግበሩንም ይከታተላል፤

፬/ በዩኒቨርሲቲው በቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብትና ጠቅላላ አገልግሎት የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት እንዲኖር ይሠራል፤

፭/ ምቹ የሥራ አካባቢ ለመፍጠር በሚደረጉ ጥረቶች ሀሳብ ያመነጫል፣ ይተገብራል፤

፮/ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ተቋማዊ አሰራር መኖሩን፤ የመንግሥት እና የመከላከያ ፖሊሲዎች መተግበራቸውን ይከታተላል፤

፯/ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚዘጋጁ የሰው ሃብት ልማት ዕቅዶችን መርምሮ ለሴኔት ያቀርባል፤

፰/ ሌሎች በሴኔትና በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሠጡትን የአስተዳደር ስራዎችን ያከናውናል፡፡

2/ Monitor the implementation of key military values and organizational cultures in the University community; when deficiencies exist, apply corrective measures and report to the University President;

3/ Prepare and approve the administration plan of the University, and monitor its implementation;

4/ Develop a technology-assisted human resource and general service data management and exchange system at the University;

5/ Generate and implement ideas in the efforts to create a conducive work environment;

6/ Monitor the existence of transparent and accountable organizational system and implementation of government and defense policies;

7/ Review human resource development plans prepared at the university level and submit them to the Senate;

8/ Carry Out such other administrative activities as may be assigned to him by the Senate and University President.

**፳፬. ስለ ተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ካውንስል መቋቋም**

፩/ በዩኒቨርሲቲው የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ምክትል ፕሬዝዳንት እና በኮሌጆች የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ዳይሬክቶሬት መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት ለማሳለጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አባላት የያዘ የዩኒቨርሲቲው የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ካውንስል ተቋቁሟል፡-

ሀ) የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ምክትል ፕሬዝዳንት--------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) ለተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ምክትል ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆኑ ዳይሬክተሮች-------------------------------------------አባል፤

ሐ) የኮሌጆች የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ አስተባባሪዎች------------------------አባል፡፡

፪/ ካውንስሉ የራሱ ጸሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫/ ካዉንስሉ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ይሆናል፡፡

፬/ ካውንስሉ የራሱን የስብሰባ ጊዜ ይወስናል፡፡

**፳፭. የተቋማዊ ልማትና ቢዝነስ ካውንስል ተግባርና ኃላፊነት**

፩/ የዩኒቨርሲቲውን የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ሥራዎች በጥናት ይለያል፣ ያቅዳል፣ ይተገብራል፤

፪/ በዩኒቨርሲቲው የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን በጥናት ያዘጋጃል፣ መርምሮ እንዲጸድቅለት ለዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ያቀርባል ሲጸድቅለትም ይተገብራል፤

**24. Establishment of Organizational Development and Business Council**

1/ To facilitate the working relationship between the organizational development and business Vice-President of the University; and the organizational development and business directorate of the colleges, the Organizational Development and Business Council of the University having the following members is hereby established:

a) Organizational development and business Vice-President-------------------------------------------Chairperson;

b) Directors accountable for Organizational development and business Vice-President----------------------------------------------Members;

c) Coordinators of the Colleges' Organizational development and Business----------------Members;

2/ The Council shall have its own Secretary

3/ The Council shall be accountable to the University Management.

4/ The Council shall decide its meeting schedule.

**25. Powers and Duties of the Organizational Development and Business Council**

1/ Identify, plan, and implement the infrastructure expansion works of the university through research;

2/ Prepare income-generating projects for the university, submit them to university management for approval, and implement them upon approval;

፫/ በዩኒቨርሲቲው የገቢ ማስገኛ ኢንተርፕራይዞችን በጥናት ያቋቁማል፣ ይመራል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፬/ የዩኒቨርሲቲው የአይሲቲ ማዕከል ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲደራጅ ይሰራል፤

፭/ የዩኒቨርሲቲው አይሲቲ ማዕከል የሚሰራቸውን የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ለዩኒቨርሲቲው ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ሳይጋጭ እንዲተገበር የአሰራር ስርዓትን ይዘረጋል፤

፮/ ከአጫጭር ስልጠናዎች፣ ከተከታታይ ትምህርት እና ከምርምር ፈንድ የሚገኙ ገቢዎችን የሚያስተዳድርበት እና የሚመራበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

፯/ ከገቢ ማስገኛ ስራዎች የሚገኝ ገቢን የሚያስተዳድርበት የአሰራር ስርዓት ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ኮሌጆች አስፈጻሚ አካላት

### ፳፮. የኮሌጅ አመራር ካውንስል ስለ መቋቋም

፩/ በዩኒቨርሲቲው ስር የሚደራጅ ኮሌጅን ሥራ በቅርበትና በበላይነት የሚመራና የሚከታተል የኮሌጅ የአመራር ካውንስል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የኮሌጅ አመራር ካውንስል የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር ---------------------------------------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) የኮሌጁ ዲኖችና ዳይሬክተሮች-----------------------------------------------------አባል፤

ሐ) የኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ-------------------------------------------አባል፡፡

3/ Establish income-generating enterprises through research at the university; lead and monitor their performance;

4/ Establish the ICT center of the university in a standard way;

5/ Develop a system of operations so that the income-generating activities performed by the University ITC center are implemented without conflicting with the service it provides to the University;

6/ Establish procedures for managing and administering incomes generated from short-term training; Continuing Education, and Research Funds;

7/ Prepare and implement an operating system to manage incomes generated from income-generating activities.

## PART THREE

## EXECUTIVE ORGANS OF COLLEGES

### 26. Establishment of the College Management Council

1/ There is hereby established the management council of the College by this Regulation that closely leads and supervises the college activities established under the University.

2/ The College Management Council shall have the following members:

a) The Executive Director of the College-------------------Chairperson;

b) Deans and Directors of the College---------------------------------Member;

c) Office head of the College Executive Director----------Member.

**፳፯. የኮሌጅ የአመራር ካውንስል ሥልጣንና ተግባር**

የኮሌጅ አመራር ካውንስል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኮሌጁን ዋና ዳይሬክተር በስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤

፪/ በዩኒቨርሲቲው እቅድ ላይ ተመስርቶ የኮሌጁን ስትራቴጂያዊ እና አመታዊ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ያጸድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፫/ የኮሌጁን በጀት ድልድል ፍትሃዊነት ያረጋግጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፬/ የኮሌጁን የትምህርት፣ የስልጠናና የምርምር ሥራዎችን ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሂዎችን እያስቀመጠ ይተገብራል፤

፭/ የኮሌጁን የሥራ ክፍሎች የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በመገምገም ላጋጠሙ ችግሮች ወቅታዊ መፍትሂዎችን በማስቀመጥ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፮/ በኮሌጁ የሥራ ክፍሎች መካከል ጤናማ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ይሰራል፤

፯/ የኮሌጁን አካዳሚክ ኮሚሽን ውሳኔዎች በመከታተል ተፈጻሚነታቸውን ያረጋግጣል፤

፰/ ሌሎች በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡ ሥራዎችን ይፈጽማል፡፡

**፳፰. የኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን መቋቋም**

፩/ የኮሌጅ አካዳሚክ ሥራዎችን በቅርበትና በበላይነት የሚከታተልና የሚመራ አካዳሚክ ኮሚሽን በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**27. Powers and Duties of College Management Council**

The College Management Council shall have the following powers and duties:-

1/ Advice the Executive Director of the College on strategic issues;

2/ Prepare, approve, and monitor the implementation of the strategic and annual plan of the College based on the plan of the University;

3/ Ensure the fairness of budget allocation of the College; and monitor its implementation;

4/ Follow up the education, training, and research activities of the College; provide support; find solutions for problems encountered and implement;

5/ Evaluate the performance reports of college departments', identify and address any issues promptly, and implement effective solutions;

6/ Work to maintain a healthy working relationship between the departments of the college;

7/ Monitor the decisions of the College Academic Commission and ensure their implementation;

8/ Carry out such other activities as may be assigned by the University President.

**28. Establishment of the College Academic Commission**

1/ There is hereby established the Academic Commissions of the College by this Regulation that shall closely lead and supervise the academic activities of the Colleges.

፪/ የኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) የኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር ---------------------------------------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) የኮሌጁ ዲኖች -------------------------------------------------------------------አባል፤

ሐ) የኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ-----------------------------------------አባል፤

መ) በኮሌጅ ዲኖች ስር ያሉ ቡድኖችና ትምህርት ክፍሎች ኃላፊዎች---------------------------------------------------አባል፤

ሠ) የጥራትና አግባብነት ቡድን ኃላፊ ----------------------------------------------አባል፤

ረ) የኮሌጁ ሬጅስትራር -----------------------------------------------------------------አባል፤

ሰ) የኮሌጅ የተማሪዎች ጉዳይ ቡድን መሪ ------------------------------------------አባል፤

ሸ) የኮሌጅ የመምህራን፣ የሴቶችና የተማሪዎች ተወካዮች -------------------------------------------------------------አባል፡፡

2/ The College Academic Commission shall have the following members:

a) Executive Director of the College -------------------------------Chairperson;

b) College Deans -------------------------------------------------------Member;

c) Office Head of the Executive Director of the College ----Member;

d) Team leaders and department accountable for College Deans -------------------------------------Members;

e) Quality and Relevance Team Leader-------------------------Member;

f) College Registrar------------------------------------------------------Member;

g) Student Affairs team leader of the College ----------------------Member;

h) Representatives of the College's Teachers, women, and students---------------------------------------Member.

## ፳፱. <u>የኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን ሥልጣንና ተግባር</u>

የኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኮሌጁን አካዳሚክ ጉዳዮች በተመለከተ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች ላይ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ተግባራዊ እንዲሆን ዝርዝር ፕሮግራሞች መውጣታቸውንም ያረጋግጣል፣ ተግባራዊ መሆናቸውንም ይከታተላል፤

፪/ የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻልን አስመልክቶ ከዲፓርትመንት የሚቀርቡ ሀሳቦችን ይመረምራል፣ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤

## 29. <u>Powers and Duties of the College Academic Commission</u>

The College Academic Commission shall have the following powers and duties:

1/ Provide ideas on short, medium, and long-term plans of the College regarding academic matters; upon approval ensure that detailed programs are issued; and follow up on their implementation;

2/ Examine ideas submitted from departments regarding improvement of the curriculum, and submit recommendations;

፫/ የዩኒቨርሲቲው የትምህርትና የምርምር ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፬/ ከረዳት ፕሮፌሰር እስከ ፕሮፌሰር ድረስ ለመምህራን የአካዳሚክ ማዕረግ እንዲሰጥ ለሴኔት ሀሳብ ያቀርባል፣ እስከ ሌክቸረር ያሉ የአካዳሚክ ማዕረጎችን አጽድቆ ለአካዳሚክ ዲን ካውንስል ያሳውቃል፤

፭/ የምርምር ተግባራት እንዲስፋፉ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

፮/ የፈተና አሰጣጥንና የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ይገመግማል፤

፯/ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመረቁ ተማሪዎችን ዝርዝር መርምሮና አጽድቆ በአካዳሚክ ዲን ካውንስል ታይቶ ለሴኔቱ እንዲቀርብ ይሰራል፤

፰/ በኮሌጁ የሚሰጡ ኮርሶች ትምህርት አሰጣጥ፣ የትምህርት መርጃዎች፣ ላቦራቶሪዎችና የማጣቀሻ መፃህፍት ወቅታዊና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ይሰራል፤

፱/ የኮሌጁ መምህራን በአካዳሚክ ዝግጁነትና በማስተማር ሥነዘዴ አተገባበር ብቃት ያላቸው መሆኑን ይከታተላል፣ አስፈላጊ የትምህርትና ስልጠና እድሎች እንዲመቻቹላቸው ይሰራል፤

፲/ እንደ አስፈላጊነቱ የተለያዩ የአካዳሚክ ሥራዎችን የሚሰሩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

፲፩/ ማንኛውንም የአካዳሚክ ሰራተኛ በአስረጂነት ይጠራል፤

፲፪/ በሴሚስተር ሦስት ጊዜ ይሰበሰባል፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎች ሊያደርግ ይችላል፤

3/ Ensure that academic and research Regulations and Directives of the University are properly executed;

4/ Recommend to the Senate the conferring of academic ranks of teaching staffs from assistant professor up to professor; approve academic ranks up to lecturer and notify the Academic Dean’s Council;

5/ Encourage and support the expansion of research activities;

6/ Evaluate examination procedures and students’ results;

7/ Evaluate and approve the list of graduating students and submit it to the Academic Deans Council for evaluation and submission to the Senate;

8/ Strive to uphold and make up to date the standard of teaching methodology of courses offered by the College, educational resources, laboratories, and reference books;

9/ Monitor the competence of teachers at the College on academic readiness and the implementation of teaching methods; facilitate them with necessary education and training opportunities.

10/ Establish different committees as may be required that perform various academic activities;

11/ Summon any academic staff as a witness;

12/ Hold meetings three times in a semester and may call extraordinary meetings as may be required:

፲፫/ ሌሎች ከዩኒቨርሲቲው አስፈጻሚ አካላት፣ ከኮሌጁ ዋና ዳይሬክተር እና ከአካዳሚክ ዲኖች ካውንስል የሚሰጡ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፴. የኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

የኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩/ የኮሌጁ ተማሪዎችና ስታፍ ሕገ-መንግሥታዊ ስርዓቱን ለማስጠበቅ የግንባታ ሥራዎች ይመራል፤

፪/ ፖሊሲዎች ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል የኮሌጁን ሥራዎች ያቅዳል፣ ስለተግባራዊነቱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፫/ የኮሌጁን በጀት በወቅቱ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በዩኒቨርሲቲው አመራር ካውንስል እንዲመደብ ያደርጋል፤ የተፈቀደውን በጀት በስሩ ላሉ ክፍሎች በዕቅዳቸው መሰረት በኮሌጁ አመራር ካውንስል እንዲመደብ ያደርጋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፬/ የኮሌጁን አካዳሚክ ኮሚሽንና አመራር ካውንስል ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፣ በጋራ የሚተላለፉ ውሳኔዎች መተግበራቸውን ይከታተላል፤

፭/ በኮሌጁ የሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎች፣ የምርምርና ስርጸት ሥራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ከሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲና ከመከላከያ ፍላጐት አንጻር የተቃኙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

13 Carry out such other activities as may be assigned by the executive organs of the University, the College Executive Director, and the Academic Deans Council.

30. **Powers and Duties of the College Executive Director**

The College Executive Director is accountable to the President of the University and has the following powers and duties:

1/ Lead capacity-building activities for students and staff of the college to maintain the constitutional order;

2/ Monitor the implementation of Policies, Regulations, and Directives; plan the college activities; monitor and supervise their implementation;

3/ Prepare the college's budget on time and facilitate its allocation by the university management council; allocate the approved budget to its departments according to their plan and monitor its implementation;

4/ Call and lead the academic commission and management council meeting of the college; and monitor the implementation of decisions;

5/ Ensure that the education and training, research, and adoption activities provided by the college are up to standard and are aligned with the country’s education policy and defense needs;

፮/ የምርምር ሥራዎች እንዲዳብሩ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ያረጋግጣል፤

፯/ በኮሌጁ የሚደረጉ ምርምሮች፣ የሚሰጡ ስርዓተ ትምህርቶችና የአካዳሚክ ፕሮግራሞች በአብዛኛው የሠራዊቱን ተልዕኮ የሚያሳኩ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፰/ ኮሌጁን በመወከል ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለዩኒቨርስቲ ሥራ አመራር ካውንስል በማቅረብ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፱/ በኮሌጁ የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀልጣፋና ፍትሃዊ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

፲/ የኮሌጁን የተቋማዊ ለውጥ ሂደት በበላይነት ይመራል፤

፲፩/ በዩኒቨርስቲ ሥራ አመራር ካውንስል፤ በኮሌጅ አመራር ካውንስልና በአካዳሚክ ኮሚሽን የተወሰኑ ውሳኔዎችን ያስፈጽማል፤

፲፪/ ስለ ኮሌጁ የሥራ እንቅስቃሴ ለዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፫/ የኮሌጁን አጠቃላይ ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፬/ በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ይፈጽማል፡፡

፴፩. **የትምህርት ክፍሎች ካውንስል ሥልጣንና ተግባር**

እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል በትምህርት ክፍሉ ኃላፊ የሚመራና ሁሉንም የሙሉ ጊዜ መምህራን ያካተተ የራሱ ካውንስል የሚኖረው ሲሆን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

6/ Ensure that an enabling environment is created for the development of research activities;

7/ Ensure that the research, education, and academic programs conducted by the college largely contribute to the achievement of the defense mission;

8/ On behalf of the college, submit issues to the University Management Council that need its decision;

9/ Monitor and ensure that the services provided by the college are efficient and fair;

10/ Lead the college's organizational development process;

11/ Implement decisions passed by the University Management Council; the College Management Council and the Academic Commission;

12/ Submit a quarterly report of the college's activities to the university president;

13/ Lead, manage, and supervise the overall work of the college;

14/ Carry out such other activities as may be assigned by the president.

31. **Powers and Duties of the Departments' Council**

Every department, led by the department head, shall have its council which includes all full-time teachers as a member; and shall have the following powers and duties:

፩/ በትምህርት ክፍሉ እንዲከፈቱ ፍላጎት የሚቀርብባቸው አዳዲስ ፕሮግራሞችን በጥናት በመለየት ለኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን ያቀርባል፤

፪/ በትምህርት ክፍሉ የሥርዓተ-ትምህርት ማሻሻያና ቀረጻ ሥራን ያከናውናል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫/ የትምህርት ክፍሉን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ሲጸድቅለትም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ የክንውን ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፬/ መምህራንና ተማሪዎችን ይገመግማል፣ ለሚፈጠሩ ችግሮችም አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤

፭/ በየሴሚስተሩ የሚሠጡ ኮርሶችን ለኮሌጁ ሬጂስትራር ያሳውቃል፣ መምህራንን ይመድባል፣ የመምህራንን የማስተማርና የምርምር ጊዜ ይወስናል፤

፮/ የማስተማሪያ ጽሁፎችን አመራረጥና ዝግጅት ይወስናል፤

፯/ በትምህርት ክፍሉ የሚሠጡ ትምህርቶችንና ፈተናዎችን ጥራት ለማስጠበቅ ከሚመለታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

፰/ የመምህራንን የአካዳሚክ ዕድገት ጥያቄ ገምግሞ ወደ አካዳሚክ ኮሚሽን ያቀርባል፤

፱/ የተማሪዎችን ውጤት ከኮሌጁ ሬጂስትራር ጋር በመሆን ይገመግማል፤

፲/ ሌሎች በአካዳሚክ ዲን የሚሠጡትን ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

1/ Based on the interest submitted by the department, conduct the necessary studies to launch new programs and submit them to the College Academic Commission;

2/ Conduct curriculum design and revision activities in the department; and implement upon approval by the concerned organ;

3/ Prepare the department's annual plan and budget; monitor its implementation upon approval; and submit a performance report to the concerned organ;

4/ Evaluate teachers and students; and provide quick solutions for problems;

5/ Report the courses to be provided every semester to the College registrar; assign teachers; and determine teachers teaching and research schedule;

6/ Determine the selection and preparation of teaching materials;

7/ Work with concerned bodies to ensure the quality of education and exams that are provided by the department;

8/ Evaluate applications for academic promotion of the teaching staff and submit them to the academic commission;

9/ Evaluate students' results together with the College registrar;

10/ Carry out such other activities as may be assigned by the Academic Dean.

## ክፍል አራት
## ስለ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት

**፴፪. የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት አስተዳደር ካውንስል መቋቋም**

፩/ የዩኒቨርሲቲውን የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት ሥራዎችን በቅርበትና በበላይነት ለመከታተልና ለመምራት የኢንስቲትዩቱ አመራር ካውንስል በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ አመራር ካውንስል የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ) የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር------------------------ሰብሳቢ፤

ለ) የምርምር ማዕከላት ዳይሬክተሮች ----------------------------------------------አባል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ ------------------አባል፡፡

**፴፫. የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት አስተደደር ካውንስል ሥልጣንና ተግባር**

የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት አስተዳደር ካውንስል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

፩/ ስትራቴጂያዊ በሆኑ ጉዳዮች የኢንስቲትዩቱን ዋና ዳይሬክተር ያማክራል፤

፪/ ለተቋሙ የተመደበውን በጀት በተገቢውና በፍትሃዊነት ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፫/ በኢንስቲትዩቱ የሚሠሩ የምርምርና ስርጸት ስራዎች የመከላከያንና የሀገሪቱን ፍላጎት ያሟሉና ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፤

## PART FOUR
## RESEARCH AND DEVELOPMENT INSTITUTE

**32. Establishment of Research and Development Institute Management Council**

1/ There is hereby established the Management Council of the institute by this Regulation that shall closely lead and supervise activities of the Research and Development Institute of the University.

2/ The Institute Management Council shall have the following members:

a) Executive Director of the Research and Development Institute-----------------------------------------Chairperson;

b) Research Center Directors--------------------------------------------Members;

c) The Institute’s Executive Director Office head-------------------Member;

**33. Powers and Duties of Research and Development Institute Management Council**

The Research and Development Institute Management Council shall have the following powers and duties:

1/ Advise the Executive Director of the institute on strategic matters;

2/ Follow up on the proper and equitable utilization of the budget allocated for the institute;

3/ Ensure that the research and adoption activities of the institute meet the needs of the defense and the country, and are of the highest quality;

፬/ የምርምርና ልማት የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፭/ የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎችን የደረጃ ዕድገት ጥያቄ እስከ አሶሼት ተመራማሪ ድረስ ያሉትን መርምሮ ያጸድቃል፣ ከአሶሼት ተመራማሪ በላይ ያሉ ጥያቄዎች ለሴኔት ቀርበው ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፮/ የኢንስቲትዩቱን የሥራ ክፍሎች የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ይገመግማል፣ ላጋጠሙ የአፈጻጸም ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

፯/ በኢንስቲትዩቱ የሥራ ክፍሎች መካከል የተሳለጠ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ይሠራል፤

፰/ ሎሎች ከዩኒቨርሲቲው ዋና ዳይሬክተር እና ከምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ካውንስል የሚሰጡትን ሥራዎች ይሰራል፡፡

**፴፬. <u>የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር</u>**

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩/ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል ይቆጣጠራል፤

4/ Prepare the strategic and annual plan of the research and development institute; and implement it upon approval;

5/ Examine and approve applications for promotion of the institute researchers up to Associate Professorship, for applications above Associate Professor submit the applications to the Senate for decision;

6/ Evaluate the plan performance report of the institute departments; devise and implement timely solutions for the problems encountered;

7/ Create a smooth inter-departmental working relationship within the institute;

8/ Carry out such other activities as may be assigned by the Executive Director of the University, and Research and Technology Transfer Council.

**34. <u>Powers and Duties of Research and Development Institute Executive Director</u>**

The University Research and Development Institute Executive Director shall be accountable to the University President and shall have the following powers and duties:

1/ Lead, manage, and supervise the overall activities of the research and development institute;

፪/ ለመከላከያ ዩኒቨርስቲና ለመከላከያ ከፍተኛ አመራሮች ስለ ወደፊት የመከላከያ የምርምር አቅጣጫዎች በሚመለከት ለውሳኔ የሚያመች ምክረ ሐሳብ ያቀርባል፤

፫/ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱን የሥራ ዕቅድ በማዘጋጀት በዩኒቨርሲቲው አመራር ካውንስል ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፬/ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱን በጀት ማዘጋጀት ለዩኒቨርሲቲው አመራር ካውንስል አቅርቦ ማጸደቅ፣ ሲፈቀድለትም በስሩ ላሉ የሥራ ክፍሎች በዕቅዳቸው መሰረት በኢንስቲትዩቱ አመራር ካውንስል እንዲመደብ ማድረግ እና አፈጻጸሙንም መከታተል፤

፭/ በምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱ የሚሰሩ የምርምር ሥራዎች ደረጃቸውን የጠበቁና የመከላከያን የማድረግ አቅም እና የሠራዊቱን ተልዕኮ አፈጻጸም የሚያሳድጉ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፮/ የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱ የሰው ኃይል የማቴሪያል እና ፋሲሊቲ እንዲሟላ አስፈላጊውን ጥረት እና ክትትል ያደርጋል፤

፯/ በምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱ ስም የሚደረጉ ማናቸውንም ስምምነቶች እና ሰነዶች ይፈርማል፤

፰/ የመከላከያ እቅዶችን፣ የመከላከያና የመከላከያ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም የምርምርና ልማት ኢንስቲትዩት ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በተገቢው መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፤

2/ Provide recommendations for the university and defense strategic leaders regarding future defense research Directions;

3/ Prepare its work plan; and monitor its implementation upon approval by the university management council;

4/ Prepare the Research and Development Institute's budget on time and facilitate its approval by the university management council, allocate the approved budget to its departments according to their plan and monitor its implementation;

5/ Monitor and supervise that the research works carried out by the Research and Development Institute are up to standard and enhance the defense capability and the execution of the army's mission;

6/ Make the necessary efforts and follow up on the fulfillment of the Research and Development Institute human resources, materials, and facilities;

7/ Sign any contracts and documents on behalf of the Research and Development Institute;

8/ Supervise the proper implementation of the defense plans, and the university and research and development institute Policies, Regulations, and Directives;

፱/ በምርምርና ልማት ኢንስቲትዩቱ ስር ያሉ የምርምር ማዕከላት የሚያከናውኗቸውን የምርምር ሥራዎች የሥራ አፈጻጸም በየወቅቱ እንዲገመገም ያደርጋል የግምገማውን ውጤትም በአግባቡ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፲/ የአስተዳደራዊ ጉዳዮችን በመመሪያው መሠረት መፈጸማቸውን ይቆጣጠራል፡፡

**ክፍል አምስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፴፭. በጀት**

የዩኒቨርሲቲው በጀት የሚከተሉት ምንጮች ይኖሩታል፡-

፩/ ከመንግሥት ከሚመደብ በጀት፣

፪/ ዩኒቨርሲቲው ከሚያመነጨው የውስጥ ገቢ፣ እና

፫/ ከሌሎች ምንጮች ይሆናል፡፡

**፴፮. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ዩኒቨርሲቲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**፴፯. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ ከዚህ በፊት የነበረው የሀገር መከላከያ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፰/፩ሺ፱፻፺፫ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ይህንን ደንብ የሚቃረን ሕግ፣ መመሪያ እና አሰራር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

9/ Periodically evaluate the performance of the research works conducted by the research centers under the Research and Development Institute, and ensure that the results of the evaluation are being properly implemented;

10/ Supervise the implementation of administrative matters in accordance with the Directive.

**PART FIVE**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**35. Budget**

The budget of the University shall be drawn from:

1/ Budget allocated by the Government;

2/ Internal revenue generated by the university; and

3/ Any other sources.

**36. Books of Accounts**

1/ The University shall keep complete and accurate books of account.

2/ The books of account and financial documents of the University shall be audited annually by the Auditor General or by other auditors designated by him.

**37. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ The National Defense University College Establishment Council of Ministers Regulations No. 68/2001 is hereby repealed.

2/ No Law, Regulations, Directives, or Practices shall, in so far as they are inconsistent with the provisions of this Regulation, have effect with respect to matters provided for by this Regulation.

**፴፰. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

፩/ ከዚህ በፊት ሥራ ላይ በነበረው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፰/፩ሺ፱፻፺፫ መሰረት በማድረግ ዩኒቨርሲቲው ያወጣቸው ሌሎች የማስፈጸሚያ ሕጎች እና አሰራሮች የዚህን ደንብ መውጣት ተከትሎ እስኪሻሻሉ ድረስ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

፪/ ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ዩኒቨርሲቲው የገባቸው ግዴታዎች፣ ውሎች እና የወሰዳቸው ኃላፊነቶች የዩኒቨርሲቲው ሕጋዊ ኃላፊነቶች ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

**፴፱. <u>አርማ እና ማህተም</u>**

ዩኒቨርሲቲው በቦርዱ የጸደቀ የራሱ አርማ እና ማህተም ይኖረዋል፡፡

**፵. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>**

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፵፩. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**38. <u>Transitional provision</u>**

1/ According to University College establishment Council of Ministers Regulation No. 68/2001, other applicable laws and procedures issued by the University may be effective until they are amended following the approval of this Regulation.

2/ Obligations, contracts, and other responsibilities undertaken by the University prior to the coming into force of this Regulation shall remain the legal responsibilities of the University.

**39. <u>Logo and Seal</u>**

The university shall have its logo and seal approved by the board.

**40. <u>Power to Issue Directive</u>**

The Ministry may issue Directives to enforce this Regulation.

**41. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force upon the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 5th Day of March,2025**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**